# ማኒፌስቶ

(ት.ህ.ነ.ኣ.ድ)

የትግራይ ህዝብ ነፃ ኣውጪ ድርጅት

የመጀመሪያ እትም

በየካቲት ወር 1968 ዓ/ም

ማውጫ


መቅድም ........................ V

መግቢያ ........................ VIII

I እሁን እካለው ሁኔታ

1- ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ........................ 1

ሀ. ፖለቲካዊ ስልጣን ........................

ለ. የፖለቲካ ነፃነት አለመኖር ........................ 5

ሐ. ብሄራዊ ተፅእኖ ........................ 7

መ. ፕሮፓጋንዳ ........................ 10

2- ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ........................ 12

ሀ. የመሬት ይዞታው ስርዓትና ችግሩ ........................

ለ. የኢንዱስትሪዎች አለመስፋፋት ........................ 13

3- ማህበረሰባዊ ሁኔታዎች ........................ 14

ሀ. ራስን መጣል [ዲ-ሁማናይዜሽን] ........................

ለ. የማህበረሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና እረፍት ማጣት 15

II መፍትሔው

ሀ. ብሔራዊ ትግል ........................ 17

ለ. የትጥቅ ትግል ........................ 21





III. አሳሳቢ ለሆኑት ውስጣዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለን አቋም ........................

1. የመሬት ጉዳይ ........................ 22

2. የከተማ ቦታና የትርፍ ቤቶች ጉዳይ ........................ 30

3. የእርሻ ጉዳይ ........................ 32

4. የአፍሪካ ኅብረት ........................ 34

5. ኢምፔሪያሊዝምና ስለተጨቋኙ ዓለም ........................ 36

6. የውጭ ጉዳይ አመራር ........................ 37

# መቅድም

ይህ መፅሐፍ የትግራይ ሕዝብ ሃቀኛ ወዳጅ የሆነው የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ድርጅት [ተ.ሓ.ህ.ት]* መግለጫና የትግሉ መመሪያ ነው። የትግራይ ሕዝብ ማለት በትግራይ ውስጥ የሚኖሩትንና በተለያዩ ምክንያት ከትግራይ መሬት ውጭ የሚኖሩትን ሕዝቦች በሙሉ ያጠቃልላል ነው። [ትግሪኛ ተናጋሪዎች፣ አፋር (ጠልጣል)፣ አገው፣ ሳሆ፣ ኩናማ፣ ወ.ዘ.ተ.] የትግራይ መሬት በደቡብ አካውና፣ በሰሜን መረብ ሲያገለግሉት በምዕራብ በኩል ደግሞ ወልቃይትንና ፀገዴን ያጠቃልላል።

ትግራይ** አክሱም እስከወደቀችበት ጊዜ ድረስ የአክሱም መንግሥት እየተገዛች ትጠራ ነበር። አክሱም ከወደቀች በኋላም እራሷን በማስተዳደር ከብዙ ጊዜ ብትኖርም ቅሉ አለቃ አለቃ ገዥዎቹ ከነበሩት ነገሥታት ግብር መክፈሏ አልቀረም።

በአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ብቻ በርትቶ ባገባቸው የነበሩትን ነገሥታት በቁጥጥር ሥር አውሎ ነበር፤ ይሁን እንጂ አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ በአፄ ምኒልክ አማካኝነት ትግራይ በሸዋ ማእከላዊ ግዛት ሥር



ወደቀች። ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው የአማራው የመሳፍንት ሉዓላዊ ተከታዮች የትግራይን ነፃነት ገፈው የሕዝቧን አንድነት ያናጉት። ግለሰና ለውር በሆነ ዘዴዎችም [እጅዋ ዘዴዎቹ] የትግራይ ሕዝብ በድንቁርና፣ በበሽታ፣ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰምጥ ያደረጉት። በተለይም ትግሬነትን በፍጥነት እንዲከስምና ይህውም በግድ አማራ ለማድረግ ያልሞከሩት ዘዴ ገድሮም መሬቷ ተቆርሶ ለተወሰደባትና የተደራረበ ጭቆና ለሆነባት አገሪቷ ትኩ ተላለፈ። ያጠቃላይ ገዢ ጊዜ ትግራይ ነፃነቷ የተገፈፈች፣ መሬቷ ተቆርሶ የተወሰደባትና የተወሳሰበ ችግር የደረሰው ሕዝብ የሚኖርባት ጭቆን ሀገር ናት።

* ተ.ሓ.ህ.ት. ግብጽ ጀነራል ማንቂቶችና አብዮታዊ ንቅናቄ በትግራይ ምድር ማካሄድ የጀመረው ከየካቲት ወር 1967 ዓ.ም ወዲህ ሲሆንም ቅሉ ከዛ በፊት የነበሩ ትግራይ ተማሪዎች ድርጅት (ብ.ት.ተ.ድ.) በሚል ስም ከለውጡት ወቅት ጀምሮ የምስጢራዊ ድርጅቶችና አብዮታዊ መዘጋጀትን አድርጓል። ይሁን እንጂ ተ.ሓ.ህ.ት. በዚህ ጊዜ

ብቻ የተፈጠረ ተጓምራቱ ቀጠለ ነበሩ፡—

(ሀ) ጥቂት የቻግራኑ ሕዝብ ከሰማንያ (80) ዓመት በላይ ቶግለ ባዳኝ ኗሪው ፍሬና —

(ለ) ተራማጅ ቻግራ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ ፀንሶቶ የነበረውን እንጋቱ ለጅ ነው።

** ስለ ጋራ ቻክክራና የቻግራዬን ታሪክ ለማወቅ
* "የቻግራኤ ታሪክ፣ መፈቷና ሕዝቧ" በሚል ርዕስ ተ.ሐ.ሀ.ቸ. ያዘጋጀውን መጽሐፍ መመልከት ይጠቅማል። —

—YOX—



## መግቢያ

የመደብ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና በሶሺያሊስት ሥርዓት ዓይነ ተራማጅ የሆኑ ሁሉ ከተጠቀሰው. ሰፊ ሕዝብ ጋር ሆነው ለተጠቃው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ ብሔራዊና ሕብረተሰባዊ ዓላማዎችን ይዞ መሠረታዊ ለውጥ (አብዮት) የማካሄድ ቅስቀሳ ኃላፊነት አለባቸው።

የጥቆታቸው ካሉ-አደሮችና ድሀ ገበሬዎች የሚያስከትል እንዲሚያደርግ ብዝበዛ ፓለቲካዊ ጭቆና ደርሶባቸው በተለያዩ ዘዴ የተቀሰ ትግል በሚያደርጉበት በአሁኑ ጊዜ ለጭቁኑ ሕዝብ የሚቆረቆሩ ተራማጆች ትግሉን የማቀናጀትና አብዮታዊ መስመሩን የማስያዝ ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው። በዚህም አቋም እንዳንቀሳቀሱ በአብዮታዊ መታደሩ በመንግሥት በመካሄድ ላይ ያለው ለውጥ ምክንያት ለደረሰ የቻለው የገበ ጭቆና ሊጠፋ የሚችለው በተደጋገመ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው። ትሁን እንጂ የተደጋገመ አብዮታዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ በማርክሳዊ-ለኒናዊ በሆነ ርዕዮተ-ዓለም በማይለወጥ አስተሳሰብ የተደራጀ አብዮታዊ ድርጅት ያስፈልጋል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የምርት ግንኙነት

መደገፍ ብዝበዛ ከማስከተሉም በላይ የብሔሮች ጭቆና እንዲኖር አድርጓል። ስለዚህ ፋሽስታዊው ወታደራዊ መንግሥት የሚያደርገው ንኡስ-ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ካለመቀበሉ፣ የብሔረሰቦች ጥያቄ ሕዝብ ነፃነት የሚገኘው በትጥቅ ትግል ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣ ታሪካዊ ግዴታን ለመፈጸም ተ.ሓ.ህ.ት. ተብሎ የሚጠራ ብሔራዊ አብዮታዊ ግንባር አቋቋመ። ይህም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት [ሕ.ዲ.አር] ወቅትም በሕብረተሰባዊ አብዮት ጊዜ የሚካሄድ ዋነኛ ብሔራዊ ትግል በመሠረቱ መደባዊ ትግል መሆኑን በማመን ነው።

ስለዚህ -

ማርክሲዝ-ሌኒንዝም ትክክለኛና ሳይንሳዊ የላብ-አደር ርዕዮተ-ዓለም መሆኑን በማመንና በአሁኑ ጊዜ የሚካሄደው አብዮት ከግቡ ሊደርስ የሚችለው ይህንን መመሪያ በማድረግ ብቻ መሆኑን በመገንዘብ:-

ብሔሮችና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በማስተዋልና ለዓላማችን መቃናት [illegible] መሆኑን በመገንዘብ ፀረ-ንኡስ ከበርቴያዊ ፋሽስትነት፣ ፀረ-ብሔራዊ ጭቆናና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም



የሆነ ፓርቲያዊ አቋም በመያዝ:-

ባገር ውስጥ በተደረገው ጠጋኝ ለውጥ ንኡስ-ከበርቴያዊ ፋሽስትነት ከዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመቀናጀት የነበረውን የብሔሮች ጭቆና ስላባባሰውና ጭቆናውም እንዳይለዝም ማድረጉን በማስተዋል:-

የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች እንደሌሎቹ ያልበለፀጉ ሃገሮች ሕዝቦች በዓለም-አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና በየሀገሩ ባሉት አድሃሪያን (በኢትዮጵያ በንኡስ-ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ፋሽስትነት) የተበዘበዙና የተጨቆኑ መሆናቸውን በመገንዘብ፤ ጭቆናውና ብዝበዛው ሊወገድ የሚችለው የላብ-አደሮችና የድሀ ገበሬዎች መደራጀት ተደራጅተውም ወዝ-አደሩ የሚመራው ቀጣይነት ታሪካዊ ተልእኮውን በመያዝ የፓርቲ ትግሉን አራምዶ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማካሄድ ብቻ ነው። ወዝ-አደሩንና ድሀ ገበሬውን ለማደራጀት በኢትዮጵያ ማርክሲዝ-ሌኒንዝም የሆነ የፓርቲ ማሕበር መቋቋም የግድ ያስፈልጋል። ይህ የፓርቲ ማሕበር በመላው ኢትዮጵያ የሚደረገውን የፓርቲ ትግል በመምራት [ብሔራዊ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ጎን

[ካሉት ብሔሮች በስተቀር] በአሁኑ ጊዜ የትግራይ ትግል ለማድረግ ጎረ ካሉት ጭቁን ብሔሮች ትግል ጋር በመተባበር ድሉን አግኝቶ መደባዊ ብዝበዛና ብሔራዊ ጭቆና ለማጥፋት የዲሞክራሲና የሕብረተሰብአዊነት መሠረት ለመጣል ብቻ መሆኑን በመረዳት:-

ቢሆንም ባገንኑት ዘመን የነበረውን የብሔሮች ቅራኔ እየተባባሰ በመሄድ እነዚህ ብሔሮች ተባብረው ባንድነት እንዳይታገሉ ማድረግ በጣም አስቸጋሪና የማያቻል ሆኖ ይገኛል። ይህ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ስሜት [በተለይ በብሔረ-ትግራይ] የመደብን ንቃት ሸፍኖት ይገኛል። ይህ ሲሆን የቻለው ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔሮች ለብዙ ዘመናት በዛቻ ተባብረው እንዲኖሩ በመደረጋቸው የተጨቆኑት ብሔሮች ጭቆናውን ሊቋቋሙት አልቻሉም፤ ከእንግዲህ ወዲህም ተገደው በህብረት መኖር የማይችሉ፤ ተጠባቂ ሁኔታ የሚያፈራርሱቸው ቢሆንም አሁን ባለው የህብረት መልክ የህብረት ትግል ለማድረግ ዝግጁና የንቃተ ህሊናቸው ምቹነት መሆኑን በመገንዘብ:-



በተጨማሪ ደግሞ የትግራይ ሕዝብ የተጨቆነ፣ የተበዘበዘ በመሆኑ ለዲሞክራሲ ፀረ-ብሔራዊ ተፅዕኖችና ፀረ-ንኡስ-ከበርቴያዊ ጠባቦች ለውጥ፣ እንደዚሁም ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም የሆነ አቋም በመያዝ ብሔራዊ የትግራይ ትግል ለማካሄድ ዝግጁ መሆኑን በማመን ነው።

የትግሉ ደረጃ መደባዊ ትግል ሆኖ ባሕሪው ግን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ይዞ ነው። ይህ አብዮት የትግሉ መጨረሻ ግብ ሳይሆን ወደ ሕብረተሰብአዊነት መሸጋገሪያ ድልድይ ሆኖ ሕብረተሰብአዊነት የሚያዝልበትን ማቴሪያል ሁኔታዎች እንዲሟሉ የሚያደርግ አብዮት ነው። ትግሉም ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ከምንም አቋሙና ከአገር ውስጥ ተራማጅ ድርጅቶች ጋር የሚተባበርና አብዮታዊ እንቅስቃሴያቸውን የሚደግፍ መሆኑን እያገለጽን፦

የሕዝባችን ተቆርቋሪዎች እንደመሆናችን መጠን በተ.ሓ.ህ.ት. ሥር ተደራጅተን የሕዝባችንን ትግል ለማነቃቃትና ብሔራዊ መስመሩን ለማስያዝ የትግላችንን ችቦ አቀጣጥለናል።

ተ.ሓ.ህ.ት.

—o—

## የተ.ሓ.ህ.ት. ትግል መነሻው፣ባሕሪውና ዓላማው የሚመለከት ተጨማሪ ማብራሪያ:-

### I አሁን ስላለው ሁኔታ:-

#### 1. ፓለቲካዊ ሁኔታዎች:-

ሀ. ፓለቲካዊ ሥልጣን. ለረጅም ጊዜ በቆየው የባላባታዊና የኢምፔሪያሊስቶች ሥርዓት ባስከተለው ፓለቲካዊ ጭቆናና ኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ ምክንያት ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝቦች በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም. አብዮታዊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በማካሄድ በተለያዩ የትግል ዘዴዎች [ሥራ በማቆም የተቃውሞ ሰልፍ ወ.ዘ.ተ. በማድረግ] የደረሰባቸውን ግፍና በደል በግልጽ አስታወቁ። ለተፈጠረው አብዮታዊ ሁኔታ መነሻ የሆነው የገዢው ጅግሮች በእርግጥ የተፈጠረው ፓለቲካዊና ወታደራዊ ሁኔታ እየከፋ መሄድ፣በብዙ ቦታዎች የረኃብ መስፋፋትና በችግሩም ምክንያት የብዙ ሕዝቦች ሕይወት መጥፋት፣ የቤንዚን የዕቃዎችን የኑሮ ዋጋ መናር ሲሆን መሠረታዊ መነሻው ግን የበሰበሰው ሥርዓትና የመንግሥት የኢኮኖሚ ውድቀት እንደዚሁም የመደቦች ቅራኔ መክረርና



መሠረታዊ የሆኑት ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሕዝቡ መነፈግ ነበሩ። እንቅስቃሴው አቋሙ ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ሆኖ ለዲሞክራሲ ለሕዝብ ተስብ ፍትሕና ለኢኮኖሚያዊ ግስጋሴ የቆመ ነበር። ጭቁኑ መደቦች በቡድን ለመታገል በቀበሌዎችና በተነቃቁበት በዚሁ እንቅስቃሴ ውስጥ የንኡስ ከበርቴው መደብ ግንባር ቀደም ፓለቲካዊ ተሳትፎ ነበረው። የእንቅስቃሴው መሪ ከበርቴያዊ መሆኑ በትግሉ ሰላምና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ግን የተሟሉ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ባሕሪይ ይዞ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ እንቅስቃሴ ከነበረው ሁኔታ ጋር የተያያዘ ሁለት አበይት ጉድለቶች ነበሩት።

### II ኛ የፓለቲካ ድርጅቶች አለመኖር

በመጀመሪያው አብዮት እንደታየው ጭቁን ሕዝቦች በሚገባ ታግለው ለማሸነፍ በመጀመሪያ መደራጀት አለባቸው። ጭቁን የኢትዮጵያ ሕዝቦች ግን ምንም እንኳን በጽናትና ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም በሆነ መስመር ቢታገሉም ትግላቸው ካላማው ለማድረስ ፓለቲካዊ መመሪያና ትክክለኛ የትግል መስመር እንዲያስተላልፉ የሚያደርግ አብዮታዊ

ዴሞክራት አልነበሩትም። ያለ አብዮታዊ ድርጅት ደግሞ አብዮታዊ ትግል ተካሂዶ ከግቡ እንደማይደርስ የታወቀ ነው።

## ፫ኛ የመሳፍንታዊ ቡድኖች መተናነቅና የንጉሡ ቃል

በዚህ ጊዜ ሕዝባዊው ትግል እያደገ የመጣበት ሕዝብ መደባዊ ጭቆና ጠብቆ በመምከል የተነሳሳ ከነዱ የመሳፍንቱ ቡድን ተቃቃመ። ቡድኑ ከወታደራዊ ባለሥልጣናት ጋር የመንግሥት ሥልጣን ለመካፈል ከንጉሡ ጋር ተስማምቶ --- ለምክር ቤቱ ብዙ ተሰጥቷቸው በዚህ መንገድ በንጉሡ ቃል ተደግፎ በአዋጅ ለሕዝብ ተነገረ። ይህም የሕዝቡን መነሳሳት ለጊዜው እንዲበርድ አደረገው።

ይህ፡ በዚህ "እንደ ሕዝባዊው እንቅስቃሴ በሰላማዊ መንገድ እመልሳለሁ" በሚል "የሥርዓት መሻሻያ" ደርግ ተቋቋመ። ደርጉ ሕዝቡን በማደናገር ለሕዝቡ የቆመ መሰሎ ባዶ የተስፋ ቃል በመስጠት ቀስ በቀስ በሞቀን የአንዳንድ ሕዝቦች ለውም የፓርቲካውን ሥልጣን ጠበቁ። ደርጉ የፓርቲካ ሥልጣኑን የያዘው ሕዝቡ ሁሉንም ዓይነት ጭቆና ባስመረረው ጊዜ ሲሆን በአብዮታዊያንና በፀረ-አብዮታዊያን መካከል ትግል ሲጠናከር ተደመረ።



የሥርዓት መሻሻያዎች መንግሥቱ ፀረ-አብዮታዊ በመሆኑ ዓላ ተሰጥቶቻቸውን እያሳጣ ሉዓላዊ ከዋጆችን እያወጣ ደምስሎ ዎ ጥያቄዎችን እየፈታ እንደሚሆንም እዚህ ላይ ያውሉን? ወጣት መሳሪያንቶም ሰይፎቹ ሥልጣን እየያዙ እንደገና ጊዜ ሉዓላዊ ጠብቆን እያጋለጠ ነበር።

ሉዓላዊ ጠብቆን ለመሸፈን ሕዝቡን እንደ የሕዝቡን ትግል ለማደናቀፍ "ህብረተሰባዊነት" መመሪያውን አሰሙ። "ህብረተሰባዊ" አዋጆች የመሬት ይዞታንና ትርፍ ቤቶችን በማስመለስ ጉዳይ ላይ ወጡ። ይህ ያለንበት ምክንያት አዋጆች ሥራ ላይ ለማዋል በቂ ድርጅት መሟላት የሚገባቸው ነገሮች በመሟላታቸው የአዋጁ መንፈስ አብዮታዊ መንገድ የተከተለ ሰይሆን የሕዝቡን ተቃውሞና የሠራ የአገሪቱ ውድቀቱ ለመውጣት የተገለሰሰ ጋሪቲክ ሴራ በመሆኑ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በደርጉ ውስጥ በቡድን የመከፋፈል በሥልጣን ሽሚያ መተናነቅ መሪዎች ጠበቅ እየሆነ መጣ። በቡድኖች መካከል ያለው ቅራኔና የሥልጣን ሽሚያ እሁንም መሪሩ ባለበት ነው። ሉዓላዊ ደርግ እያሄደነ ተራማጆችን እያሰረ እንደ ዓይነት ወንጀል የሠሩ ለማስታወቅ ለሁሉም

እንድ ዓይነት ድርጅ በመስጠት በዓለም ተወዳዳሪ የሌለው ፋሽስት መሆኑን አስመስክሯል።

ለ- <u>የፖለቲካ ነፃነት አስመልክቶ፡-</u>

በህብረተሰብ ውስጥ መደቦች እስካሉ ድረስ ሃቀኛና ትክክለኛ የሆነ ነፃነትና እኩልነት ሊኖር እንደማይችል አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊ ትግላቸውን ለማካሄድ ሁኔታው የሚፈቅድላቸው የፖለቲካ ነፃነት ማለት የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግና የመደራጀት መብት ሊሰጣቸው ይገባል። እነዚህ መብቶች ለሕዝቡ መስጠት የሚችለው በሕዝብ ለሕዝብ የቆመ የዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ብቻ ነው። ለዚህ ነው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ተራማጅ ወገኖች ፋሽስታዊውን ደርግ ለመጣል በሚያደርጉት ትግል ወደ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የሚያሸጋግራቸውን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ደጋግመው የሚጠይቁት። ይህ ጥያቄ ምንም እንኳ ጠንካራ ትግልና ረጅም ጉዞ የሚያስፈልገው ቢሆንም ታሪካዊ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ጭቁን ሕዝቦች ሳይደራጁ ቀርተው የፖለቲካ



ሥልጣን ለመያዝ በማይችሉበት ጊዜ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት በማቋቋም ሥልጣን ወደ ሌሎች አድሃሪያን ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች እንዳይተላለፍ ሊከላከሉ ይችላሉ።

በ1905 ዓ.ም. እ.ኤ.አ. በሩሲያ የተደረገው ዲሞክራሲያዊ አብዮት ምሳሌ ብንወስድ በዚያን ጊዜ በሩሲያ ውስጥ የነበረው ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅት ያሰጠው ቅዋም ያለው፤ የፖለቲካ መመሪያ ፡ መሪ ሊሆን ይችላል። መመሪያውም "የላብ-አደሩን ጥቅም ለማስገኘትና ለሶሻሊስት ሰፊ አብዮት በቂ የሆነ የፖለቲካ ነፃነት ለሚያስፈልገው

ለዚህም ከምንገነዘበው መንግሥት በዲሞክራሲያዊ መንግሥት መሠረት ስለሚያስፈልግ፤ ይህን ለማድረግ የሚችለው ደግሞ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አሸንፎ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት ከቋቋመ በኋላ መንግሥት በጊዜው ህዝባዊ ምርጫ እንዲካሄድ በማድረግ የአብዮት አካሄድና የጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት አስፈላጊነት በመመልከት ጉዳይ ለህዝብ በቂ ገለፃ ማድረግ አስፈላጊ ነው። መንግሥት የላብ-አደሩ

መብት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥያቄዎች በተቀናጀ ሥራ
ካደ እንደሚሉ ያደርጋል።" ይላል።

ይህ ፖሊሲያዊ አብዮታዊ መንግሥት ለኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች
በነፃነትም ጥያቄው ካሁንም መልስ ያገኙ የረዥሙ ውጊያ
ሆኖ ቀርቷል።

ለ. <u>በቡርዧ ተቃራኒ</u> ህብረተሰባዊያት ርዕዮተ-ዓለም።
የብሔሮች ጥያቄ በሚከተለው መንገድ ያፈታል።

"የብሔሮች የራስ ዕድል ራስ መወሰን ማለት
ተጨቋኝ ብሔር ከጨቋኝ ብሔር የፖለቲካ
መገንጠል እድርጋ ነፃ የሆነ የራሱ መንግሥት
ማቋቋም ማለት ነው። የራስን ዕድል ራስ የመወሰን
መብት የሚፈልጉትን መገንጠልን ያበረታታሉ።
ብሎ መሟገን የመፈታት መብት የሚያስጠብቅን
በተለያዩ አገሮችና ያላቸው ብሎ እንደመወንጀል
የሚቆጠር የማይጠበቁና የሞኝነት አነጋገር ነው።
ካዕለታዊ ተግባራቸው ጭቁን ህዝብ የሚገልጹ
የኢኮኖሚ ውሳኔ፤ የሶሻ አገርና ሰው ገበያ
ጥቅም በሚገባ ያውቃታል። ስለዚህ ወደ



መገንጠል የሚያመራ ብሄራዊ ተፅዕኖ ባለከተለው የብሄሮች
ቅራኔ ምክንያት በእኩልነት መኖር በማይቻል የማይቻል ሲሆን
ወይም ሆኖ ሲገኝና የኢኮኖሚ መተሳሰር እንቅፋት ሲከሰት
ሆነ ወይም ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ የከበርቴዎች
እኩልነትና የመደቦች ቀጣይ ነፃነት በበከጠ ሊከሰት የሚችል
ሆኖ በመገንጠል ብቻ ነው። የራስን ዕድል ራስን የመወሰን መብት
መገፈፍ ማለት የጨቋኙ ብሔር ጥቅም መጠበቅ ማለት ነው።"
ሌኒን

በተጨማሪም ሌኒን የመገንጠል እኩልነትን ሲገልጽ፡—
"የሶሻሊስት በራስ መደብ መከፋፈል ለማጥፋት የተጨቆኑ
መደብ እምነትን እንደሚያስፈልግ ሁሉ የሚቃወም
የብሔሮች መሟሟላ ሊገኝ የሚችለው መሸጋገሪያ በሆነው
የብሔሮች ነፃነት። ማለት የብሔሮች መገንጠል መብት
ሙሉ በሙሉ ሲኖር ብቻ ነው።" ይላል።
እንግዲያውስ በዚህ መሰረት የአማራ ብሔር በትግራይ
ሕዝብ ላይ የምታደርገው ተፅዕኖ እንመለከት፤ በኢትዮጵያ
ያሉት ጭቁን ብሄሮች በተለይ ብሄረ-ትግራይ በጨቋኝ
አማራ ብሄር የሚደርስባቸው ተፅዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ

እየሰፋና እየተባባሰ በመሄዱ በብሄሮች መካከል አለመተማመ
ማንና መጠራጠርን አስከትሎአል። ይህ በመሆኑ የኢትዮጵያ
ጭቁን ሕዝቦች በሙሉ በአንድነት ሆነው መደባዊ ትግሉን
ለማካሄድ ከማያስችላቸው ደረጃ ደርሷል። በተለይ በየጊዜው
እየከረረና እየተባባሰ በመሄድ ላይ ባለው የብሄሮች ትግል
ምክንያት የጨቋኙና የተጨቋኙ ብሄሮች ሶሻሊስቶች በዚህ
ጉዳይ ላይ አስፈላጊ የሆነ ውይይት፣ መረዳዳት፣ ሃቀኛና
ጠንካራ የሆነ አንድ ዓይነት አቋም ሊይዙ አልቻሉም።
ይህ ሊሆን የቻለው የብሄረ አማራ ሶሻሊስቶች ትምክህተኞችና
አድርባዮች ሆነው ለሰለሚገኙ ነው። በተለማጆች መካከልና
በጭቁን ህዝቦች መካከል ያለው መለያየት ለመንግሥቱ ጥሩ
አጋጣሚ ሆኖለት እየመረጠ እንዳሻውም ሊጫወትበት።
ለዚህ ጭቁን ብሄሮች ከብሔራዊ ተፅዕኖና ከማንኛውም
ዓይነት ብዝበዛ ነፃ ለመውጣት መደባዊ መፍትሄ ያለው
ብሔራዊ የትግል ትግል ማድረግ ሃቀኛና ትክክለኛ ሆኖ
እናገኘዋለን። ብሔር-ትግሉንም ጭቁን ብሔር በመምራት
ከሰፊ የተጋለጠውና የአብዮት መንገድ መርጦአቸዋል።



መ- <u>ፕሮፓጋንዳ</u>:- ተስፋ ብቻ ያዘሉ ፍሬቢስ ባዶ አዋጆችና
መግለጫዎች በየጊዜው ይሰራጫሉ። እነዚህ ከእውነት የራቁ
መግለጫዎችና ዲስኩሮች በመገናኛ መስመሮች በጭቁን
ህዝብና በሀገር ሰም ይታወጃሉ። የአዋጆቹ ዓላማ
የህዝቡን አስተሳሰብ ለማደናገርና ወታደራዊ ደርግ በሥ
ልጣን ላይ ለመቆየት ያለው ፍላጎት እንደዚሁም በድርጊ
ጥቅም ለመጠበቅ ሆኖ ተብሎ የሚደረግ የፕሮፓ
ጋንዳ ነው። ፋሽስታዊው መንግሥት የኢኮኖሚ ውድቀት
ለደጋገመው ችግሩን ለመወጣት ፋብሪካዎችና ኩባንያ
ዎችንና የከተማ ቤቶችን እንደዚሁም ግዛቶችን በቁጥጥሩ
ሥር የሚያደርግ አዋጅ አወጣ። በኤርትራ ውስጥ
በሚያደርገው ጦርነትና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርገው
ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ደርጉ ፋሽስታዊ ተግባሩን
ለማካሄድ ገንዘብ ስላጣ የግብር አዋጅና የሕዝብን
ንብረት በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል። ከዚህም በላይ
የሕዝቡ ፖለቲካዊ ተቃውሞ በርትቶ መንግሥቱንና ሰደና
ጋው ፋሽስታዊ አዋጆችን ያውጃል። ለተመጣኙም
የህዝቡ ተቃውሞ ጠንክሮ የመንግሥቱ አቋም በመዳከሙ

ጊዜ ሕዝቡን በማታለል አንዳንድ መፈክሮ አቀናጅቶ ያውጃል
ፋሽስታዊ ጠባዩ እየተገለጠ በሄደ ቁጥር ይህንን ጠባዩ
ለመሸፈን በግብር ሊገልፅ የማይችል የወረቀት አዋጅ
ያውጃል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳን እነዚህ ባዶ
ፕሮፓጋንዳዎች ለጊዜው የህዝቡን አስተሳሰብ ሊጠመዝ
ዙ ቢችሉም በመጨረሻ የደርግ ፋሽስታዊነትና አድሃሪ
ጠባዩ መገለጹ አልቀረም።

ቁጣ:- ተራማጆችንና አድሃሪዎችን አንድ ዓይነት ክስ
እንዲቀርብባቸው በማድረግ አንድ ዓይነት ፍርድ እንዲቀ
በሉ ተደርጓል። በተጨማሪም 'ተራማጅ' አቋማችን
ተቃውሞአችኋል በሚል ርካሽ ምክንያት ተራማጆችን ለማጥ
ፋት ፋሽስታዊው ደርግ የሚያደርገው ፀረ-አብዮታዊ
ድርጊት ለማንም ግልጽ ነው። ይህም ምንም እንኳ የሕዝ
ቡን የሀሳብ ፍርድ ለጊዜው ቢያወናብድም ውሎ አድሮ እውነተ
ኛው መገለጹ አልቀረም። የውሸት ፕሮፓጋንዳ የህዝቡን አስተያየት
ብዙ ጊዜ አወናብዶ እንደማይኖር የታወቀ ነው።
እንደነውም የደርግ አድሃሪ ጠባይ በይበልጥ እየተገለጠ
ሄዶዋል።



## 2. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች

ሀ- የመሬት ይዞታው ሥርዓትና ጅማሬ። በኢትዮጵያ
ውስጥ የመሬት ይዞታው ሥርዓት አብዛኛው መሰረታዊ
ርስት ነው። ርስት በቤተሰብ ይዞታ የሚካሄድ ትውልድ
ቁጥር ማለትም [illegible] የመሬት ይዞታ ሥርዓት ስለሆነ በዚህ
መንገድ የጋራ ይዞታ ነው ለማለት ይቻላል። ከጠቅላላው
ህዝብ ዘጠና ከመቶ የሚሆነው ዕለታዊ ተግባሩ ሙሉ
በሙሉ በእርሻ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ መሬት ተከፋፍሎ
ተቆራርሶ ይገኛል። እንደዚሁም የግል መሬትና ገለት አለ።
ይህ ሁኔታ ያመጣ ችግር መፍትሄ እንዳያገኝ በመጀመሪ
መረዳት የሚያስፈልግ ነገር አለ። ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ
መሬት እርስ ለመኖር ብቻ ሳይሆን በይበልጥ የተወገኝ
ነት ምልክት ስለሆነ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው ዋጋ
ከፍ ያለ መሆኑን ነው። ስለዚህ የመሬት ይዞታው
ሥርዓት ለመለወጥ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት የመሬ
ይዞታ ለውጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ማስተማርና
ማስረዳት በቅድሚያ መደረግ ካለባቸው አበይት
ጉዳዮች አንዱ ነው። እንደዚሁም የገበሬዎች የፖለቲካ

ፍላጎት እንደነበራቸውና የዐጼዎ ጠንታቸውን ተግባራው
እንደመከቱ ማስረጃዎች ያሳልፋል። በተጨማሪም በከተ
ማና በገጠር ያለው የሥራ እጦት ችግር ለማቃለል
የገጠር እንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ከፍኝ መሰረታዎችን
መግዣና ማስፋፊያ መንግሥት የገንዘብና ማተሪያል
እርዳታ ማቅረብ በተጨማሪ ሊፈጸሙ የሚገባቸው
ሥራዎች ናቸው። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቀዳሚ
ነገሮች ሳይፈጸሙ ማንኛውም እቅድ መፍትሔ ሊሆን
አይችልም። ደርጉ እነዚህነገሮች ሳይሟሉ በእቅድ ሃሳብ
ከመጠቀምበመረዳት የነበረው ችግር እንዲገባስ አድርጓ
ታል። ይህ ተግባር ጊዜውን ያለተከተለና ደርጉ ፋሽስታዊ
ጠባዩን ለመሸፈን ሆነ ብሎ ያደረገው ነው። ስለዚህ የደርጉ
መንግሥት መንኮታኮትና ሥልጣን ወደ ህዝብ ማስተላለፍ
የማይቀር አስፈላጊ ተግባር ሆኖ ይገኛል።

ለ- የእንዱስትሪዎች አለመስፋፋት

ትግራይ ምቅን ብኑር በመሆንዋ በመንግሥት
የተደገፈ ወይም በግል የተያዘ እንዱስትሪ ወይም ፋብሪካ
ሊኖራት አልቻለም። እንዱስትሪዎች አዲስአበባ ውስጥ
[የጨቋኙ ብሔር ዋና ከተማ] ተከማችተው ይገኛሉ።



በዚህ ምክንያት የከተሞችን አለመስፋፋትና የሥራ አጦችን
ቁጥር ማነስ በግልፅ ይታያል። የኢኮኖሚ እድገትና የህብ
ረተሰቡ ፍላጎት ከፍ እንዳያል አድርጎታል። ለእንዱስትሪዎች
አለመስፋፋት ምክንያት የሆነው የመንግሥት መመሪያ
አድካሚ ስለሆነ ነው። የትግራይ ሕዝብ ከወያኔ ያገኘው እነስ
ተኛ ገቢ ከፍተኛ ግብር ቢከፍልም ለእንዱስትሪዎች
ማስፋፊያ የተደረገለት የመንግሥት ድጋፍ የለም።
ባካባቢያዊ የሆነው የመሬት ይዞታ ሥርዓትም ለእንዱስት-
ሪዎች አለመስፋፋት እንዱ ምክንያት ነው። በተጨማሪም
ፋሽስታዊ መንግሥት ሥልጣን ላይ ለመቆየት ብዙ
ገንዘብ ለወታደሮች መመ ለትጥቁ ስለሚያወጣው ከትግራይ
ህዝብ ብዙ ገንዘብ በግብርም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ
ገፍፎ፣በመውሰዱም ላይ ነው።

3- ሕብረተሰባዊ ሁኔታዎች፡-

ሀ- ክሰን መጠበ (ዲ-ሁማናይዜሽን):- ከቀን ወደ
ቀን እየተባባሰ የሚሄደው የኢኮኖሚ ብዝበዛ በሰፊ
ው የትግራይ ህዝብ ላይ ድህነትን፣ረሃብና ዐርዳት
እየተደጋገመ እንዲደርስ አድርጓል። በተጨማሪም

የትግራይ ህዝብ ለረጅም ዘመን ሰብዓዊና ፓለቲካዊ መብቱ ተነፍጎ ሲጠጋና ሲናቅ እንዲሁም አድልዎ ሲፈጸምበት ቆይቷል። ይህም በደል ጨቋኝዋ የአማራ ብሔር ሆነ ብላ እንደመንግሥቷ መመሪያዋ አድርጋ ስትሰራበት የቆየች ሲሆን ፋሽስታዊ ደርግም በባሰ በመረረ መንገድ ቀጥሎበታል። ከዚህም የተነሳ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ኑሮው እንደቆረቆዘ ተደርጓል። በዚህ ምክንያት የሥራ ማጣት ችግር፣ ስርመጣትና ስደትን ከማስከተሉም በላይ ለሰን መጣልና መንከራተት የትግራይ ሕዝብ ዕለታዊ ተግባሩ ሆኖ ይገኛል። ስለሆነም ሕዝቡ ተጠርጣሪና የተጠጋ እንዲሆን በመደረጉ በህብረት መኖር የማይቻል ሆኖ ይገኛል።

ለ. የህብረተሰቡ ወደ ኋላ መቅረትና ስራፈት ማጣት:

ሰፊው የትግራይ ህዝብ ሥራ አጥቶ በስርመጣትና በስደት ወ.ዘ.ተ. ብቻ ሳይሆን በረኃብ፣ በድንቁርናና በበሽታ እየተሰቃየ ይኖራል። እነዚህም ችግሮች ወንጀል እንዲፈጸም ያገፋፉታል። ስለ ትግሉ መሠረታዊ ምክንያት ሲያጠናክሩ ያልቻለዘመና ባሕላዊ



ሥርዓት ይሁኑ እንጂ ጨቋኝዋ የአማራ ብሔር የምታደርገው የኢኮኖሚ ብዝበዛና የፖለቲካ ጭቆና ተከትለውበት ነው። ከዚህም በላይ የሚያስከትለው የህዝባችን ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲዳከምና ተዳክሞ እንዲጠፋ ወይም የአማራ ብሔር የገዢ መደብ ጥቅም እንዲጠብቅ የ፲፻ ዓመታት ታሪክና ባህላችን መመጠኛዎችና መገለጫዎቹ ሆኖ ይገኛል። ይህ የታሪክ ሰርቆት በእንዲህ በኩል የአማራው ብሔር መገለጫ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ እንደሌለው ሕዝብ እንዲያስቆጥረው የታለመ የመንግሥት መመሪያ ነው። ስለዚህም የትግራይ ህዝብ ፊደሉንና ተውፊቱን በጽሑፍ በጥንቃቄ በብዙ መንገድ ይጠብቅ ገልጿል። ይህና ይህን የመሳሰሉ አድሃሪ ድርጊቶች አሁን ያለው ፋሽስታዊ መንግሥትም ስለቀጠለበት ሰብዓዊ ክብሩና መብቱ እስከ መለስ ድረስ ሰፊው የትግራይ ህዝብ ትግሉን አስፋፍቶም። ጨቋኝዋ የአማራ ብሔርም ጭቆናዋ እስካልተወገደ ድረስ ህብረተሰባዊ እረፍት አታገኝም።

## II መርሆታችን:-

### ሀ- ብሔራዊ ትግል

ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ጭቆና እና በደል አሰቃቂ ጭቆናውንና በደሉን ከሥሩ ለመንቀል የፓለቲካና የትጥቅ ትግል ሲያካሂድ ቆይቷል። በተለይም ከምኒልክ ዘመነመንግሥት ጀምሮ ፀረ-ሸዋዊ የመሳፍንቶች ሥርዓትና ፀረ-ብሔራዊ ተፅዕኖ የሆነ የተደጋገመ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አካሂዷል። ለምሳሌም በወያኔ ጊዜ ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ተጽእኖ ያካሄደው ዲሞክራሲያዊ የትጥቅ ትግል ምንጊዜም የማይረሳ ነው።

ስለዚህ:- ፩ አሁን ያለው አድሃሪ መንግሥት የብሔሮች ጭቆና በሚመለከት ጉዳይ ላይ ያለው አድሃሪ አቋም የነበሩትን የብሔሮች ጭቆና እንደገባሱና እንዲከር ስላደረገው:-

፪ እየተጋባሱና እየከረሩ የሄዱት የብሔሮች ጭቆና ጨቋኝና ተጨቋኝ ብሔሮች ለአንድ ዓላማ እንዲታገሉና መደባዊ ሥምረታቸውን እንዳያሰፉ ትልቅ እንቅፋት ስለሆነ:-



፫ኛ ምንም እንኳን አብዮት ለማካሄድ መሰረቱት የቆየ ጭቁን ህዝብ ተሳታፊ የሚሆኑበት የፓርቲና ማህበር አለመኖሩ በሆነም 'ተራማጅ' ነን ባዮች የሸዋ ምሁራን ትምክህተኞችና አድርባዮች ሆነው ስለሚገኙ በአንድ የፓርቲና ማህበር ሥር ተራማጅ ዓላማ ይዞ አብዮት ለማካሄድ የማይቻል ስለሆነ:-

ብሔራዊ ጭቆናና ተከትለው አገዛዝና ኢምፔርያሊዝምን ለመታገል ጭቁን ብሔሮች መደባዊ ይዘታቸውን ያልለቀቀ አብዮት (ብሔራዊ የትጥቅ ትግል) ማካሄድ አስፈላጊና ታሪካዊ ግዴታቸው ሆኖ ያገኙታል። ስለዚህ ነው ጭቁን የትግራይ ህዝብም አብዮታዊ ብሔራዊ የትጥቅ ትግል በማካሄድ ላይ ያለው።

### ሀ- ዓላማውና ሥራው።

የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንዑስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ለውጥ ነው። ስለዚህ የአብዮታዊው ትግል ዓላማ ከበዝባዥ ሥርዓትና ከኢምፔሪያሊዝም ነፃ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ማቋቋም ይሆናል።

ሰ- <u>የአብዮቱ ጠባዮች</u>፦ በመሠረቱ የአብዮቱ ጠባይ ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓት፣ ፀረ-ንዑስ ከበርቴያዊ ጠጋኝ ከውጭ፣ ፀረ-ብሔራዊ ተፅእኖና ፀረ-ኢምፔርያሊዝም ከመሆኑም በላይ የራሱን ዕድል ራሱ የመወሰን መብት በመደገፍ ለዴሞክራሲና ለነፃነት የሚታገል አብዮት ነው። ባጭሩ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት [ኤን.ዲ.አር] ነው። የአብዮቱ መሠረታዊ ኃይሎችም ከድሀ ገበሬዎች፣ ከላብ-አደሮችና ከተቀሩት ንዑስ-ከበርቴዎች እንዲሁ-ም ከሌሎች ብሔራዊ ስሜት ካላቸው ክፍሎች ይመሠ-ጫል።

ትግሉ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት በመሆኑ የአዲሱ ዴሞክራሲ ፕሮግራሞችን እንደ ፕሮግራሙ አድርጎ ተቀብሏቸዋል። ይህን ለመመርኮዝ ተ.ሓ.ህ.ት. ኢኮኖሚ-ያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሕብረተሰብኣዊና ባህላዊ ዓላማዎችን እንደሚከተለው ያገልጿል።

<u>በፖለቲካ</u>:— ፀረ-ባላባታዊ ሥርዓትና ፀረ-ኢምፔርያ-ሊዝም የሆኑት ኃይሎች በሙሉ የዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ያቋቁማሉ። መሠረታዊ የዴሞክራሲ መብቶች



ለጭቁን መደቦች ያለ ምንም ገደብ ይሰጣሉ። ህዝቡ በመንግሥቱ ሥልጣን ተሳታፊ እንዲሆን ተወካዮቹን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይመርጣል። <u>ሥልጣኑም የጭቁን መደቦች ይሆናል</u>። ሕዝባዊው መንግሥት የሕዝቡ ድህንነት የመጠበቅና የመደብ ጠላቶችን የመርገጥ ኃላፊነት ይኖረዋል። ይህም ማለት ዴሞክራሲያዊ መንግሥቱም በዴሞክራሲያዊ ማእከላዊነት [<u>ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም</u>] የተመሠረተ የአስተዳደር ዘይቤ በመከተል የሕዝቡ ሙሉ ተወካይነት አምኖ የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የ[illegible]ነሮች ወ.ዘ.ተ. ልዩነት እንዳይኖር ማድረግ ማለት ነው።

<u>በኢኮኖሚ</u>:- መሠረታዊ ሰለተ-ምርት ዲሞሰስና የኢምፔርያሊዝም ብዝበዛ ከሥሩ ነቅሎ ነፃ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ማቋቋም የመሬት ይዞታውን ሥርዓት ማስተካከል ከበርቴያዊ ምርት ተቆጣጥሮ የምርት ኃይሎችን በህብረተሰቡ ቁጥጥር ሥር በማድረግ ለህብረተሰባዊነት ኢኮኖሚ መንገድ መጥረግና የህዝቡን ጥቅም ለሚፃረ ሳት ማንኛውንም ዓይነት ብዝበዛ የሌለበት የኢኮኖሚ ሥርዓት መመሥረት የተ.ሓ.ህ.ት. የማይታጠፉ ዓላማዎች

የቻው። ጊዜው ያለፈበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ባስከተለው ብዙ ብዙ ምክንያት በሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉት መሠረታዊ ችግሮች፦ ድንቁርና፣ በሽታ፣ ድህነትና ረሃብ የመሳሰሉ እንዲዚሁም መደቦችና የመደብ ብዝበዛ ለማጥፋት ተ.ሓ.ህ.ት. የማያቋርጥ ትግል ታደርጋለች።

በባህል፦ አሁን ያለውን አሮጌና አድሃሪ ባህል ደምስሶ በአዲሱ አብዮታዊ ባህል መተካት የተ.ሓ.ህ.ት ዓላማ ነው። ይህም ባህል ፀረ-ብዝበዛና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ባህል ከመሆኑም በላይ በመደብ ይዘታው የፆታና የንኡስ-ብሔሮች ልዩነት የሌለበት በላብ-አደር ዓለም-አቀፋዊነት ላይ የተመሠረተ የዕድገትና የእኩልነት ባህል ይሆናል።

ሰ- የትጥቅ ትግል፦ ከላይ የተገለጹት ዓላማዎችን በሥራ ለመተርጐም ትግሉ በማርክሲዝም-ሌኒኒዝም-ማኦ-ሴቱንግ ርእዮተ-ዓለም የሚመራ ዘመናዊ ያልፈጠ ውጊያ ታክቲክና ስትራቴጂ የተላበሰ እንዲዚሁም ብሔራዊ መንግሥት ለመቋቋም የሚታገልም በጭቁን የትግራይ ሕዝብ የተደገፈ የትጥቅ ትግል ሆኖ እናገኘዋለን።



## III አሳሳቢ በሆኑት ውስጣዊና ዓለም-አቀፋዊ ሁኔታዎች ላይ ያለን አቋም።

1- የገጠር መሬት ጉዳይ፦

የገጠር መሬት ጉዳይ በመላው ኢትዮጵያ አሳሳቢ የሆነ የኢኮኖሚ ችግር በመሆኑ በቶሎ መፍትሔ ማግኘት አለበት። ችግሩ የጭቁን ህዝብ ችግር በመሆኑ ለብዙ ጊዜ ተራማጆችን ሲያሳስብ የኖረ አሁንም አብዮታዊ መፍትሔ የሚጠብቅ ጥያቄ ነው። ባላባታዊው የመሬት ይዞታ ሥርዓት ለጥቂቶቹ መሳፍንቶች ምቾት ሲሰጣቸው ለሰፊው ህዝብ ግን መከራን ድህነትንና ረሃብን አስከትሏል። እንዲሁም ጭሰኛው ከእርሻ የሚያገኘው ገቢ እያነሰ በሄደ ቁጥር በዚህ አንፃር ደግሞ የሚከፍለው ግብር ከመጠመሩም በላይ በየጊዜው እየናረ የሚሄደው የዕቃዎች ዋጋ ኑሮው እየቆረቆዘ እንዲሄድ አድርጎታል። 'መሬት ላራሹ' የሚለው ዲሞክራሲያዊ የህዝብ መፈክር የመሬት ይዞታን ችግር መፍትሔ እንዲያገኝ የሚጠይቅ ነው። መፈክሩ ተደጋግሞ በህዝቡ ይጠቀስ እንጂ ችግሩ

እስካሁን ድረስ መሠረታዊ መፍትሔ አላገኘም።

ባካባታዊ ሆኖ በዝምድና ላይ የተመሠረተው ርስት የሚባለው የመሬት ይዞታ ያስከተለው ችግር በትግራይ አሁን ያለው ሁኔታ በመመልከት መረዳት እንችላለን። መሬት በጊዜ ብዛት እየተቆራረጠ ለአንድ ሰው ወይም ቤተሰብ በተለያዩ ቦታዎች ይሰጠዋል። የዚህ ዓይነቱ የመሬት ሥርዓት ትርጉሙ በእርሻ ላይ በተመሠረተ ህዝብ ላይ ግልጽ የሆነ የእርሻ ችግር አስከትሏል።

እንደ በተገለጹው ምክንያቶችና ተፈጥሮ ባስከተላቸው ችግሮች ከእርሻ የሚገኘው ገቢ እያደረ ሲቆረቆዝ የህዝቡ ብዛትና የሚከፍለው ግብር (ታክስ) ግን እያደረ ስለሚጨምር ሕዝቡ በየጊዜው በረሃብ ይሰቃያል። በተጨማሪም በመሬት ክርክር ምክንያት በየፍርድ ቤቱ ይንከራተታል። ብዙ ሰውም አገሩን ለቆ ወደየከተማው ይሰደዳል። ከተማ ገብቶ ሥራ ስለማያገኝ ሴቶች ወደ ሽርሙጥና (ሴት አዳሪነት) ሲያመሩ ወንዶቹ ደግሞ ወደ ሌብነትና ማጅራት መችነት ያመራሉ። የቀሩት ቁጥራቸው ከ-እስከ ሊገለ የማይቻል ሰዎች በረሃብና በበሽታ



ያልቃሉ። ስለዚህ ይህንን ከባድ ችግር በምን ዓይነት መፍትሄ ሊገኝለት ይገባል? የሚል ጥያቄ ያጋጥመናል። ችግሩ በአብዮታዊ መንገድ መፍትሄ ሊያገኝበት የሚችል ፕሮግራም ሁሉ ጎኑ የሚከተሉትን ሥራዎች ማካሄድ ይገባዋል።

1ኛ የገባርነትን ኢኮኖሚያዊ መሠረት ማጥፋትና ገባሮቹ መሬት በመደብ-ብነት እንደገና ማደል።

2ኛ ለህብረተሰብ ጎጂ ርዳታ መንገድ መጥረግ። እነዚህ ሥራዎች ማካሄድ ማለት ደግሞ ጭሰኛና ጉልተኛነት ማጥፋት፣ የመሬት ይዞታን ማስተካከል፣ የህብረት እርሻ ማስፋፋት፣ ጥቃቅን ወዝ-አደር ማደራጀትና ፖለቲካዊ ትምህርት መስጠት ማለት ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም የመሬት ክርክር ማጥፋት። በየገጠሩ የሚገኘው የሥራ ማጣት ችግር ማቃለል። በእርሻ ላይ የተመሠረተ ትንንሽ እንዱስትሪዎች ማቋቋም አስፈላጊ ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች እሥራ ላይ ለማዋል የሚቀጥሉት ነገሮች በአንድነት መሟላት አለባቸው።

1ኛ አስፈላጊው የፖለቲካ መስመርና መመሪያ ከሰፊው ህዝብ የሚሰጥ፣ የሰፊው ህዝብ ጥቅም በእውነት የሚጠብቅ በላብ-አደሩ የሚመራ ጊዜያዊ አብዮታዊ መንግሥት

ማቋቋም።

2ኛ ፕሮግራሙ እሥራ ጎደ ለማግኘት የሚያስፈልገ ያሰው፣ የገንዘብና ወይም ሌላ የማንኛውም ማቴርያል ዝግጅት ማጠናቀቅ።

በዚህ አንፃር አድሃሪው <u>የንኡስ-ከበርቴ</u> <u>መንግሥት</u> ያለውን ችግር እንዴት ለማቃለል እንደሞከረ እንመርምር። መንግሥቱ በዚህ ረገድ ባወጃቸው አዋጆች አንፃር ሰንመ- ለከተው የመሬት ይዞታ ችግርንና ባሕሪ-ሃሳባዊ መፍትሔው የገባው ይመስላል። ጠለቅ ብለን ስንመረምረው ግን መፍትሄው በመሬቀት ብቻ ተወስኖ እንዲቀር የታሰበ መሆ- ኑን እንገነዘባለን። ዋናው ቁምነገር ደግሞ ብሔራዊ መፍትሔው ማወቅ ብቻ ሳይሆን ችግሩን ለመፍታት አብዮታዊ ፍላጎትና ስሜት መኖሩ ነው። ይህ ማለትም አስፈላጊ የሆኑት ፓለቲካዊ፣ ድርጅታዊ፣ የገንዘብና የሰው ኀልበት ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማሟላት ነው።

አዋጁ ስለ----፡

1. <u>ርስት</u>

ሀ. በዚህ ሥርዓት ውስጥ የሚገኘው መሬት የሚያዙትና



የሚያከውጥ ስለሆነ ለህዝቡ የመኖር ዋስትናና ክብርን ለጥቶ እንደቆየና አብዛኛው ህዝብ ከምን ጊዜ በጭሰኝነት እንደሚተዳደር ግልፅ ነው።

ለ- የኢትዮጵያ ህዝብ ሕብረትና ወንድማማችነት በበለጠ ለማጠናከር በኢትዮጵያ የሚገኘው የመሬት ይዞታ አንድ ማድረግ ያስፈልጋል። በአስተዳደርም በኩል በሆን ለአንድ አገር ህዝብ ተመሳሳይ ሕግ ማውጣት ጠቃሚ ነው፡ ይላል።

ይህ ጉልታዊ ሥርዓት ለህዝቡ የመኖር ዋስትና ለጥቶታል ብሎ ማወጅ ሥርዓቱ የፈጠረውን ግልፅ ድህነትና ረሃብ መካድ ማለት ነው። ግልፅ የሆነ የመደብ ቅራኔና ልዩነት እያለ አብዛኛው ህዝብ በጭሰኝነት እንደሚተዳደር ግልፅ ነው ብሎ ማለት ችግሩን ለማጥቃት ብቻ ሳይሆን መሠረቱ ለሌለው ህብረትና ወንድማማችነት ተብሎ ከተለያየ የመሬት ይዞታ ችግር አንድ ዓይነት አዋጅ ማወጅ መንግሥቱ ለማ ወናበድና ለማጭበርበር የሚያደርገውን ሙከራ ግልፅ አድርጎ ያሳያል። ስለችግሩም አብዮታዊ መፍትሄ ለማግኘት ስሜትና ፍላጎት እንደሌለው ያስረዳል።

2. የገበሬዎች ማሕበሮች በአዋጁ መሠረት ሥራና ዓላማቸው

እንደሚከተለው ተዘርዝሮ እናገኘዋለን።

<u>ዓላማ</u> ሀ- "በህብረተሰባዊ ፍልስፍና መሠረት የጭሰኞችና የድሀ ገበሬዎች ፖለቲካዊ መብትና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመጠበቅና ለማስፋፋት"

ለ- "ህብረተሰባዊነትን ሥራ ላይ ለማዋል በሚደረገው እርምጃዎች ተካፋይ እንዲሆኑ ከህብረተሰቡ ተራማጅ ክፍሎች በተለይም ከላብ-አደሩ ማህበሮች ጋር መተባበርና መተሳሰር።"

<u>ሥራ</u> ሀ- "ዐዋጁ የግል ይዞታ በሆነባቸው ቦታዎች ሁሉ መሬቱን በትክክልና ያለአንዳች አድልዎ ለጭሰኞችና ለድሀ ገበሬዎች ማደል።"

ለ- "በርስትና በዘሳን መሬቶች ላይ አስፈላጊ የሆኑት የህብረት ሥራዎችንና ድርጅቶች ማካሄድ።

ሐ- ማደራጀት፣ ምርጫ ማካሄድ፣ ፖለቲካ ትምህርት መስጠት፣ የፖለቲካና የአስተዳደር ሥራዎች ማካሄድ የአካባቢው ሕብረተሰባዊ ሕጋዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ማቃለል።"

ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሱትን አበይት ጉዳዮች



ለማካሄድ የተወሰኑ ድርጅቶች የተቋቋሙት በደንብ ባልተደራጀ መንገድ የፖለቲካ ንቃታቸው በጣም ዝቅተኛ በሆነ የሥራ ልምድ በሌላቸው ወታደሮችና በዘመቻው በሚያምኑ ተማሪዎች እንዲሁም ባካባቢው ሚቃ ሹሞች ነው። መሠረታቸው የሚያገኙት ከዚህ ይባስ ብሎ ደግሞ ይህ የማደራጀትና ፖለቲካዊ ትምህርት የማካሄድ ሥራ የሚከናወነው ጥቂት የአድሃሪው መንግሥት ካባሮች 'ደርግ' ባወጡት መመሪያ መሠረት ነው። እነዚህ ጥቂት አወናባጆች ህብረተሰባዊነትን የሚያውቁት በቃል እንጂ በግብር ካለመሆኑንም በላይ ይህ የሚያሳፍር እውቀታቸውንም በሥራ ለማወናበድ እንጂ ቁምነገር ለመሥራት አይጠቀሙበትም። በተጨማሪ ደግሞ አድሃሪው ደርግ የኢትዮጵያ ላብ-አደሮች ኮንፌደሬሽን አውድሞ በምትኩ አድሃሪ የሆነ የላብ-አደሮች ማህበር እንዲመሠረት በማድረጉ የተባለው የሠራተኛው ማህበር መሠረት ነክቶት ይገኛል። ይህ የሚያሳየን እነዚህ የገበሬ ማህበሮች በወረቀት ላይ የሠፈረውን ዓላማና ሥራ በግብር ለመተርጎም ሳይሆን የተባለው ዓላማና ሥራ በወረቀት ላይ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር

የመንግሥት ወኪሎች ሆነው የመንግሥቱ ሥራዎችና ፍላጎት ለማሟላት መመሰረታቸው ነው። ስለዚህ የጭሰኞችና የድሀ ገበሬዎች የፓለቲካና የኤኮኖሚ ፍላጎት ለማሟላት አልተመሠረቱም ማለት ነው።

3- <u>ታጣቂ ኣርሻዎች</u>፡- አዋጁ ስለነዚህ ኣርሻዎች

ሀ- የመንግሥት ኣርሻዎችና የህብረት ኣርሻዎች እስኪደራጁ ድረስ መንግሥቱ እነዚህን ታጣቂ ኣርሻዎች በመሰለው መንገድ ያስተዳድራል። በተጨማሪም መንግሥት በመሰለው መንገድ እስኪያስተዳድራቸው ድረስ የእነዚህ ታጣቂ ኣርሻዎች ባለቤቶች ማስተዳደራቸውን ይቀጥላሉ።

ለ- በየመሥሪያ ቤት እንዲሰራ የተሰጠው መግለጫ መሠረት ደግሞ እነዚህን ታጣቂ ኣርሻዎች በመካፈል የሚፈልጉ ገበሬዎች የሉም በሚል ምክንያት እነዚህ ኣርሻዎች ለባለቤቶቹ ወይም ለሌላው ሰው በኪራይ ሊሰጥ እንደሚችል እንገነዘባለን። በተጨማሪም የተወረሱት ታጣቂ ኣርሻዎች ያስተዳድርና የቴክኒክ ጉድለት ይፈጠራል በሚል ምክንያት በማህበር መንግሥታዊ ቀርቶ በመንግሥት ሥር እንዲተዳደሩ ተደርጓል።



መንግሥቱ ታጣቂ ኣርሻዎችን በመሰለው መንገድ ያስተዳድራል የሚለውን ሃሳብ በደርጉ አነጋገር ስንመለከተው ደርጉ እነዚህን ኣርሻዎች ለኢምፔሪያሊስቶች በኮንሰሲዮን ሊሰጣቸው እንደሚችል እንረዳለን። ስለዚህ አድሃሪው መንግሥት አዋጁን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማሟላትና ለማሟላትም ስለማይችል የመንግሥቱ መውደቂያና በተራማጅ መንግሥት መተካት አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።

<u>የከተማ ቦታና የትርፍ ቤቶች ጥያቄ</u>.

ያንጋዳች ጥርጥር በሌላ ኢትዮጵያ የሚገኙት የከተማ ቦታዎችና ቤቶች በጥቂት መኳንንት፣ ከበርቴዎችና ቡችሎቻቸው እጅ ስለዚህ 2ሉ ቀድሞ ተይዘው ስለዚህም የቤት ኪራይ፣ የከተማ ቦታ ዋጋና የቤት ማሠሪያ ዋጋ በየጊዜው ከመጠን በላይ እየናረ ስለሄደ በከተማው ሕዝብ ላይ ታላቅ ውድቀትን አስከትሏል። እንደዚሁም እነዚህ የገዢው መደብ አባሎች መጠን የሌለው የግል ንብረትና ከዚሁ የሚመነጩ መብቶች አግኝተዋል። ከዚህ ጋር ነፃ አገልግሎታቸውም በላይ ባስፈለጋቸው 2ሉ ያስፈልጋቸውን ኃይል በመጠቀም የፓለቲካ ሥልጣን አግኝተው ሕዝቡን

ለመርገጥና ለመበዝበዝ ተጠቂ መውበታል። በዚህ ምክንያት አብዛኛው የከተማ ህዝብ የከተማ ቤትና መሬት የማግኘት መብቱ ተነፍጎ በቤት ኪራይ ተሰቃይቷል። በዚህ ጊዜ ነው ለእንደዚህ ዓይነት ችግር አስፈላጊ፣ ትክክለኛና የማያዳግም መፍትሔ ሊፈለግ-ለት የሚገባው፤ ይሁን እንጂ አድሃሪው መንግሥት ችግሩን በሕዝቡ ፍላጎት መሠረት በማጥናት ፋንታ ከጥቂት ገዢዎች ፍላጎትና ደስታ አኳያ ለማየት ከኖሮ ጋንጋዱ ጥቅም ብቻ አዋጅ በማውጣት ችግሩ እንዲባስ ቀጥሏል። ይህንን ለማሳት የቻልነውም:-

1ኛ መንግሥቱ ባወጣው አዋጅ ምክንያት የቤቶች ሥራ እንዲሰተሰ መበጉጥትና ይህም የእንሱተን የኢኮኖሚ ዕድገት ወደኋላ የሚጎትት ሆኖ በመጥፋቱና የቤቶች ሥራ እንዲሰተሰ በመንግሥት ወይም በሕዝቡ ማህበሮች የሚካሄድበትን መንገድ ተዘጋጅቶ ባለመቅረቡ ነው። ይህም ሲሆን የቻለው የከተማ ቤትና ቤት በጥቂት ሰዎች እጅ በመውደቁ ይህንን ታላቅ ሥራ ለማካሄድ የመንግሥት ተካፋይነት አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ሆኖም መንግሥቱ በዚህ ረገድ ፈጽሞ አልተዘጋጀም።

2ኛ ይህ የቤቶች ሥራ መቋረጥ በቀጥታ ከሚመለከታቸው



ሠራተኞች [ግምበኞች] ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድም ከቤት ሥራ የሚያገኙ ዕቃዎች በሚሠሩ ፋብሪካዎችና ድርጅቶች ውስጥ ያሉትንም ሠራተኞች የሥራ ማጣት ችግር አስከትሎባቸዋል። ከዚህ አልፎም በ1-2 ክፍል ቤት ውስጥ ይኖር የነበረው ቤተሰብ ከመንግሥቱ ጋር ባነሳው አልህ ምክንያት ጉ-ዩክፍሎቹን ስለያዘ በየከተማው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ ኑሮውን በሆቴል ውስጥ መሰረቶ ከድሮው በባሰ ቁጥ በሌለው ምዝመዛ ሲሰቃይ ይገኛል።

3ኛ ከጊዜ ወደጊዜ አየናሪ በሚሄደው የዕቃዎች ዋጋ አንፃር ሰንመለከተው የቤት ኪራይ ለመቀነስ የተወሰደው እርምጃ የማያዳግም መፍትሔ ሳይሆን ጊዜያዊ እርጥባን ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ የሚያሳየን እንደዚህ ዓይነት የተደራረበና ከባድ ችግር ሊወገድ የሚችለው በአንድ አዋጅ ሳይሆን ከሰፊው ህዝብ የመነጨ የሰፊው ህዝብ መንግሥት ሲመሠረት ብቻ ነው።

## የኤርትራ ጥያቄ

የኤርትራ ጥያቄ መንስኤው ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ መሠረታዊ መልስ ለመስጠት የሚከተሉትን ታሪካዊ መረጃዎች መመልከት

ያስፈልጋል።

ሀ- ሁለት ህዝቦች፣ሀገሮች ወይም ብሄሮች በተለያየ ጊዜ የነበራቸውን አስተዳደር ይዘው ቆይተው አንዱ ግዴ ሲይ የሚያደርገው በሃይል የተደገፈ ግዛት የቅኝ አገዛዝ ተግባር ነው።

ለ- እንዲሁም ሁለት ሀገሮች በሁለቱም ፈቃድና ፍላጎት የየግላቸው መብት ጠብቀው ከተባበሩ በኋላ አንደኛው ሌላውን ሲያምጽ አርገውኛው የቅኝ አገዛዝ አርጋዊ ነው።

እንደ በተጠቀሰው ታሪካዊ ሂደት መሠረት የኤርትራ ጉዳይ ስንመረምር የሚከተሉት ነገሮች ያጋጥሙናል።

ሀ- ገ 1890 ዓ.ም. አካባቢ ኤርትራና ኢትዮጵያ ለየብቻ- ቸው የተለያየ አስተዳደር ይዘው ይኖሩ ነበር። ይህውም ኤርትራ እንደ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ አንድ ነፃ አገር ሆነው ይኖሩ ነበር።

ለ- በ1952 ዓ.ም. ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደሬሽን መተዳደር በጀመረችበት ጊዜ ሁለቱም ሀገሮች ፌደሬሽኑ ስምምነትና የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ኤርትራ ራሷን የቻለች አገር መሆንዋን ይጠቅሳል።



ሐ- ይሁን እንጂ በ1962 ዓ.ም. ኢትዮጵያ በኤርትራ ላይ የወሰደችው እርምጃ ስምምነቱን "አንደኛው ወገን ብቻ ከተባበሩት መንግሥታት ሳይጠይቅ ሊጥሰው አይችልም።" የሚለውን ሕግ በጣሰ የዐዊ ዓሊር ሆኖ ይገኛል።

ስለዚህ ኤርትራ ውስጥ የሚደረገው ትግል ያንጓጓዥ ጥርጥር ሃቀኛና ታሪካዊ መሠረት ያለው ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ነው።

<u>የኢትዮጵያ አብዮት</u>

ሀ- በአሁን ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ሁኔታዎች ስንመረምር ህዝባዊ አብዮት ከፀረ-አብዮታዊ ደርግ ጋር ብርቱ የትንንቅ ትግል በሀገሪቱ ላይ መሆኑን እንገነዘባለን። ንኡስ-ከበርቴያዊ ፋሽስታዊ ደርግ መላው የኢትዮጵያ የፓለቲካ ሥልጣን ወብጦ ነፃው ዜጎች ተራማጆችን በጣም በመግደል ላይ ይገኛል። ህዝቡን ከመደራጀትና አብዮታዊ ለመምራት ተንኮል ያዘሉ ባዶ አዋጆችን እያወጀ ፀረ-አብዮታዊነቱን ለመሸፈን ሞክሯል። ሆኖም ይህ ተንኮል ውሎ አድሮ በመጋለጡ ህዝቡ ከአብዮታዊ ግስጋሴው ፍንክች አላለም። ምክንያቱም የደርጉ ባዶ አዋጆች የሰፊውን ህዝብ አብዮታዊ ጥያቄዎች ሰካል መከሩና

ለመለሱም የማይችሉ ስለሆነ ነው። የሰፊው ህዝብ ፍላጎት ለማሟላት የማይችለው በቡርዡዋ ዲሞክራሲያዊ ብቻ ነው።

ሉ- ከዚህ የተመሰቃቀለ ኑሮ መውጫ በር ማለት ነው። ደኸውም የብሔሮች የትጥቅ ትግል ወይም በሠፊ ኢትዮጵያ የሚካሄድ ህዝባዊ ትግል ማካሄዳቸው። የትኛውን መንገድ መከተል እንደሚገባ የሚወስነው ግን በየቦታው የሚገኘው ተጨባጭ ሁኔታ ነው። ሁለቱም መንገዶች የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት አመራር ተከትለው ሰፊውን ህብረተሰባዊነትን ለመገንባት ዓላማ አላቸው። እነዚህ ሁለት የትግል መንገዶች ተግባራዊ ሥራቸውን እንዳያካሂዱ አብዮታዊያን ነገዶች የአማራ ብሔር ትምክህተኝነትና ጠባብ ብሄርተኝነት ያጠቃቸው ሰዎች አግደውት ይገኛሉ። "ለህብረተሰባዊነት ሲባል" ከደርግ መተባበር ያስፈልጋል በማለት "ቀድሞ የነበረውን የመንግሥት ስርዓት ሙሉ በሙሉ ባይወድም አዲስ ህብረተሰባዊ ሥርዓት መመሥረት አይቻልም።" የሚለውን ታሪካዊ ማርክሳዊ ሃቅ ይክዳሉ። የተለያዩ ብሔሮች እየሄዱ ባሉት ጊዜ ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ለታገሉ ይችላሉ። በማለት በጊዜው ባለው



ተጨባጭ ሁኔታ ያልተደገፈና የአማራን ብሔር ሞቶና በሽፍንፍን ለማቆየት የታለመ የትምክህተኞች ተንኮል ደግሞ በሌላ በኩል ነው። እነዚህ የእኩ ሰቃዩንት አወናጅነታቸው እንዳይነቃባቸው በታሪክ የተደገፉትን የብሔሮች ትግል በሰዉ ጠባብ ብሔርተኝነት ለማሳሰሉ ይታያሉ። እንደዚህ ዓይነቱ አጉል መሰሪቆችና ? ትምክህተኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊያደናቅፉትና ሊያዳክሙት ቢሞክሩም። በአሁኑ ጊዜ ሰፊው ህዝብ ተደራጅቶ አብዮት ለማካሄድ ቢነሳ ፊት ለፊት እንዲህ መጋፈጥና አጉል መሰሪቆቹ በህዝብ ላይ የተፈፀሙ ታላቅ ታሪካዊ ክህደት ነው።

## ኢምፐርያሊዝምና ሦስተኛው ዓለም

በዓለም አቀፍ አድሃሪነት ለአብዮታዊ ግስጋሴዎች እንቅፋት የሆነው ኢምፐርያሊዝም የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦችን በእጅ አዙር ለመግዛትና ለመጠቀም ካለ ያለው በየአገሩ ካሉት ቡችሎች በመተባበር ነው። ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ የሚያካሂደው አሁንም እየተባለ ከኢምፐርያሊስት አገሮችና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች [የዓለም ባንክ] የዓለም የገንዘብ ድርጅት [አይ.ኤም.ኤፍ] በሚሰጠው የተሸፈነ

መርዙ አቋሙ በተዛባ የንግድ ልውውጥና ጥሬ ሀብቶቹን ያለአግባብ በመዝረፍ ነው።

ፓለቲካዊ ጭቆናውም የሚያካሂደው በዓለም ዙሪያ ባቋቋማቸው ወታደራዊ ሠፈሮችና በውጭ ጉዳይ አመራሩ ነው። የሦስተኛው ዓለም ህዝቦች በኢምፐርያሊዝምና በየአገሩ በሚገኙት ሎሌዎቹ ላይ ግልጽ ጦርነት ካወጁ ቆይተዋል። የነዚህ ሕዝቦች ትግል በየቀኑና በየሰዓቱ ወደ ድል በመቃረብ ላይ መሆኑ የማያጠራጥር ነው። ካምቦድያ፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ ሞዛምቢክ አንጎላም ወ.ዘ.ተ. በኢምፐርያሊዝም ላይ ያገኙት ድል ኢምፐ-ርያሊስቶቹን አዳክሟቸዋል። ይህ የኢምፐርያሊዝም ውድቀት ዓለም አቀፍ አብዮትና የህብረተሰብዓዊነት ድል ማለት ነው። የኛ ትግልም ከነዚህ ህዝቦች ትግል ሊነጠል የማይችል ተራማጅ ትግል በመሆኑ ከነዚህ ጭቁን ህዝቦች ትግል ብዙ እንማራለን። የጋራ ጠላቶቻችንንም በማጥፋት ህብረታችንን እንገልፃቸዋለን።

<u>የውጭ ጉዳይ አመራር</u>

እላይ እንደተገለጸው ሁሉ እንቅስቃሴያችን የዓለም ህብረተሰብዓዊና ደሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች አካል ነው።



ስለሆነም ለዓለም አቀፍ ኢምፐርያሊዝም ያለው ጠንካራ ተቃውሞና ከተራማጅ እንቅስቃሴዎች ያለው ድጋፍና ተባባሪነት ያገለግላል። በውጭ ጉዳይ አመራሩ የወዝ-አደር ዓለም አቀፋዊነት ይከተላል። ጠባብ ብሄርተኝነትና ትምክህተኝነት በጽኑ ይቃወማል።

ስለዚህ ተ.ሓ.ህ.ት

1- ካገንዳች የፓለቲካ ተጽዕኖ ከግለሰቦች፣ ወይም ከማህ-በሮች እንዲሁም አገሮች የሚሰጠውን ማንኛውም የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በደስታ ይቀበላል።
2- ቅኝ አገዛዝን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝንና ኢምፐር-ያሊዝምን በመቃወም ላይ የሚገኙትን አፍሪካዊያን ወንድሞችን መደገፍ ብቻ ሳይሆን ከነሱ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ትግሉን ያካሂዳል።
3- ፅዮናዊያንና ኢምፐርያሊስቶችን በተለይም የአሜሪካ ኢምፐርያሊስቶችን በመቃወም ላይ ከሚገኙት ፍልስጤማዊያንና የዐረብ ህዝቦች ጋር ግንኙነቱን ያጠነክራል።
4- የሮዴሽያንና የደቡብ አፍሪካን ዘረኛ መንግሥታት

በጥብቅ ያወግዛል።

5. ለዲሞክራሲና ለህብረተሰብአዊ ዕድገት በመታገል ላይ ለሚገኙት የላቲን አሜሪካና የእስያ ህዝቦች ያልተቆጠበ የሞራል ድጋፉን ይሰጣል።

ፋሺስታዊ ደርግ ይውደም!

ኢምፔሪያሊዝም ይንኮታኮት!

ድምቀት ለዓለም ተራማጅ ሃይሎች!

የትግራይ ህዝብ ትግል ያሸንፋል!!

## [illegible] ቅኑዕ ብሄራዊ ቃልሲ መደባዊ ቃልሲ እዩ፣

## Genuine National Struggle is in ESSENCE Class Struggle

ኣብ ጭቁናት ብሄራት ካብ ዝርከብ ህዝቢ ብዝኸፍአ ዝሳ
ቐየ ኣቶም ዝምዝመዙ ርዱእ- ሰራሕተኛታት ሓረስቶትን ከምኡ'ውን
ካልኦት ብሸቕሊ ዝናበሩ እዮም:: ካብዚ ድማ ብሄራዊ ጭቆና መደባዊ
ጭቆና ምዃኑ ለክዝርኣየና--- ኣንጻር ብሄራዊ ጭቆና ዝግበር
ቃልሲ'ውን ኣንጻር መደባዊ ጭቆናን ኣንጻር መድሓርሓርትን
ጠለምትን ተወካሲ ናይቲ ብሄር ዝግበር ቃልሲ ምዃኑ
ዘይጠራጠር ሓቂ እዩ::

Among the people of the oppressed nationalities, those who actually suffer are mainly the oppressed and exploited classes, the workers, peasants and other labouring classes. From this we can see that national oppression is in reality class oppression, and that the struggle against national oppression is in reality a struggle against class oppression, and often simultineously a struggle against the reactionaries and traitors of one's own nationality.

ተ.ሓ.ህ.ት.



ብሄራዊ ማዕርነትን ምሉእ ናጽነትን ንምርካብ ውፁዕ ህዝቢ ትግራይ ብተ.ሓ.ህ.ት. ተሰሪዑ ዘሎ ብሄራዊ ዲሞክራስያዊ ቃልሲ ብምክያድ ነቲ ኣሰካሕኳሒ ዘሎ ብሄራዊ ጭቆና ሃፀያዊያን ምዝኻት ከሎኹ ሮግዞም ብምፍላስ እዩ:: ከምኡ'ውን መደብ መግዛእትን ኣርዓት ዝምዝመዝን ክብሩኑ ንምብርዓቕ ኣብቲ ሃሉኡ ናብ ሶሻሊስታዊ ቃልሲ ኣሰጋጊሩ ናይ ቀርነት ክተ ክንጎምጎም'ዩ::

Inorder to achieve national equality and total emancipation, the oppressed people of Tigray nationality, under the guidance of T.P.L.F. will resolutely carryout national democratic revolution, put an end to the national oppression of the imperialists and over-throw the rule of their lackeys; they will then carry through the Socialist revolution and destroy all the exploiting classes and systems.

T.P.L.F.

—xxxoxxxoxxx—